OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# 2023 የኪነቶች በፓርኮች ውስጥ መመሪያዎች

***<u>የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ</u>***

የሲያትል የኪነጥበብ እና የባህል ቢሮ (ARTS) በከተማው ውስጥ በሚገኙ መናፈሻዎች ሁሉ ውስጥ የኪነጥበብ እና የማህበረሰብ ዝግጅቶችን ለማሳደግ ከሲያትል ፓርኮች እና መዝናኛ ጋር ሽሪክ እየሆነ ነው። በ **ኪነቶች በፓርኮች ውስጥ (Arts in Parks) ፕሮግራም** ከተማዋ በመላው ሲያትል ውስጥ ሁሉ እና በተለያዩ ማህበረሰቦች እየተካሄደ ላለው ደማቅ የባህል ስራ ውስጥ መዋዕለ ንዋይ ታደርጋለች።

ይህ ፕሮግራም በከተማው ውስጥ ከተገቢው በታች አገልግሎት ሲሰጣቸው በነበሩ እና በኢኮኖሚያዊ ውስንነት የታቀቡ ብቁ የሆኑ የሲያትል መናፈሻ አካባቢዎችን ለማንቃት የሚፈልጉ የአጎራባች የጥበብ ምክር ቤቶችን፣ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ቡድኖችን እና የግል አርቲስቶችን ይደግፋል። ይህ የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ኪነጥበቦችን እና ባህላዊ ተሳትፎን የሚያስተዋውቁ/የሚያበረታቱ አዲስ እና በደንብ የተቋቋሙ የበዓላት አከባበሮችን ወይም ክስተቶችን፣ ብዝሃነትን የሚያከብሩትን፣ የማህበረሰብ ግንኙነቶችን የሚገነቡትን፣ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን፣ አካል ጉዳተኝነቶች ያላቸው ሰዎችን፣ አዲስ ሰፋሪ እና ስደተኞችን፣ እንዲሁም የስደተኞች ማህበረሰቦች እና የቀለም ማህበረሰቦችን ጨምሮ በስርአታዊ ጭቁና ከተጎዱ ማህበረሰቦች ጋር በማገናኘት በኪነጥበብ እና ባህል በኩል ፓርኮችን እያነቃቃ ይደግፋል።

| | |
|---|---|
| **ማመልከቻ**<br>ማመልከቻው በመስመር ላይ ይገባል። ማመልከቻው በሲያትል ከተማ የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ማስገቢያ በኩል በFLUXX በ [https://seattle.fluxx.io/](https://seattle.fluxx.io/) ላይ ይገኛል<br><br>ኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት መዳረሻ ከሌለዎት ሰራተኞችን በተቻለ ፍጥነት ያግኙ። | **በመክፈት ላይ**<br>ማክሰኞ፣ ጥቅምት 4 ቀን 2022 ከጥዋቱ 9:00 (ፓስፊክ)<br><br>**የሚያበቃበት**<br>ማክሰኞ፣ ህዳር 15 ቀን 2022፣ ከምሽቱ 5:00 (ፓስፊክ) |
| **የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች:** ስለ ፕሮግራሙ አጠቃላይ እይታ ይቀበሉ እና ምርጥ የሆነ ማመልከቻ እንዴት እንደሚያስገቡ።<br><br>**አውደ ጥናት 1**<br>ረቡዕ፣ ጥቅምት 12፤ ከምሽቱ ከ5:30 – 7።<br>በመስመር ላይ ወይም በጄፈርሰን የማህበረሰብ ማእከል<br><u>እዚህ ይመዝገቡ</u><br><br>**አውደ ጥናት 2**<br>አርብ፣ ጥቅምት 21፤ ከሰዓት ከ12:30 – 2።<br>በመስመር ላይ ወይም በጄፈርሰን የማህበረሰብ ማእከል<br><u>እዚህ ይመዝገቡ</u> | **ካለቀጠሮ የሚገቡ ክፍለ-ጊዜዎች:** እነዚህ ከማመልከቻ ስርዓቱ ጋር ድጋፍ የሚያገኙበት የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜዎች ይሆናሉ።<br><br>**ካለቀጠሮ የሚገባ ክፍለ ጊዜ1**<br>ሐሙስ፣ ህዳር 3፤ ከምሽቱ ከ5:30 – 7።<br>በመስመር ላይ ወይም በጋርፊልድ የማህበረሰብ ማእከል<br><u>እዚህ ይመዝገቡ</u><br><br>**ካለቀጠሮ የሚገባ ክፍለ ጊዜ 2**<br>ረቡዕ፣ ህዳር 9፤ ከሰዓት ከ12 - 1:30።<br>በመስመር ላይ ወይም በጋርፊልድ የማህበረሰብ ማእከል<br><u>እዚህ ይመዝገቡ</u> |

*ለእርዳታ፣ ያግኙ:*

- ***ማመልከቻ ወይም መዳረሻ*** አሌክስ ሮዝ (Alex Rose) በ(206) 459-6517 ወይም alex.rose@seattle.gov። TTY፡ 711 ወይም (800) 833-6384፣ ለዓይነ ስውር ቴሌ-ብሬይል፡ (800) 833-6385

- ***የመስመር ላይ የቴክኒክ ድጋፍ*** ማርሾን ዎከር (Marshonne Walker) (marshonne.walker@seattle.gov) ወይም ማርጎ ሮብ Margo Robb (margo.robb@seattle.gov)

## ***ብቁነት/ መስፈርቶች***

**አመልካቹ** የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- አርቲስት ግለሰብ፣ የሰፈር ኪነቶች ምክር ቤት፣ ወይም የአካባቢ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ ቡድን መሆን
    - ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፣ አካል ጉዳተኞች ሰዎች፣ አዲስ ሰፋሪ እና ስደተኛ ማህበረሰቦች እና የቀለም ማህበረሰቦችን ጨምሮ እጅግ በስርአታዊ ጭቆና የተጎዱ ማህበረሰቦችን የሚወክሉ ድርጅቶች እና አርቲስት ግለሰቦች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።
- የፌዴራል የታክስ መታወቂያ መለያ ቁጥር ያለው እና በሲያትል ከተማ ውስጥ የተመሰረተ መሆን።
    - የሚያመለክቱ ቡድኖች በ501(c)(3) ለትርፍ ያልተቋቋሙ መሆን አይጠበቅባቸውም ወይም የገንዘብ አያያዝ ወኪል መጠቀም አይጠበቅባቸውም።

**ፕሮጀክቱ** የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- አንድ ጉልህ የሆነ የኪነ ጥበብ እና የባህል ይዘት ያለው፣
- ለህዝብ ነፃ እና ክፍት የሆነ፣
- ዋስትና/ ኢንሹራንስ ያለው፣
- ከበቂ በታች የመረጃ/ የቁስ ሀብት ላላቸው አርቲስቶች እና ማህበረሰቦች መድረክ የሚያቀርቡ፣
- የሲያትል ፓርክ እና መዝናኛን ተልእኮ የሚያከብሩ (ለመጫወት፣ ለመማር፣ ለማሰላሰል፣ ማህበረሰቡን ለመገንባት እና መሬቱን የመንከባከብ ኃላፊነት የተሞላበትን አገልግሎት ለማሳደግ የእንኳን ደህና መጣችሁ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እድሎችን ለመስጠት)፣
- ከሚያዝያ 1 እስከ ህዳር 30 ቀን 2023 መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ብቁነትን ያገኘ የሲያትል መናፈሻ ውስጥ የተካሄዱ።
    - በመሃል ከተማው ወይም በመሃል ከተማ መናፈሻዎች ወይም በመጫወቻ መስኮች (Playfields) እና ከማህበረሰብ ማእከላት ወዲያውኑ ቀጥሎ ያለው አረንጓዴ ቦታዎች ላይ የሚደረጉ ዝግጅቶች ጋ ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነትን **ያላገኙ**።

ለዚህ ፕሮግራም በዓመት አንድ ማመልከቻ ብቻ ማስገባት ይችላሉ።

## ***የገንዘብ ድጋፍ***

የድጋፍ ገንዘብ የተሰጣቸው ድርጅቶች ለአንድ (1) አመት የኪነቶች በፓርኮች ውስጥ (AIP) የገንዘብ ድጋፍ (በ2023 ላሉ ከንውኖች) ያገኛሉ: የአርቲስት ክፍያዎች፣ የግብይት እና የማስተዋወቂያ ክፍያዎች፣ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የሰራተኞች ወጪዎች፣ አቅርቦቶች፣ የመሳሪያ ኪራዮች ወይም ሌሎች ከምርት ጋር የተያያዙ ወጪዎች፣ አስፈላጊ ፈቃዶች፣ እና ከ 10% የማይበልጥ ከምግብ ጋር የተያያዙ ወጪዎች። የድጋፍ ገንዘቦች ለገንዘብ ማሰባሰብ፣ ለስጦታዎች፣ ከፕሮጀክቱ ጋር ወይም ከመሳሪያ ግዢ ጋር በቀጥታ ካልተገናኙ ለድርጅታዊ የአስተዳደራዊ ወጪዎች መጠቀም አይችሉም። ለዚህ ፕሮግራም ከፊል የገንዘብ ድጋፍ የለም እና ለ 2023 በበጀት ማፅደቅ ላይ ጥገኝነት ያለው ነው። አመልካቾች ለሚከተሉት የገንዘብ ድጋፍ ደረጃዎች ማመልከት ይችላሉ:

- $1,300 ዶላር (ክስተት ማካሄዳቸው ምንም ያለፈ የተያዘ መኖር አያስፈልግም)
- $2,600* ዶላር
- $5,200 ዶላር
- $7,800** ዶላር

**ከ$2,600 ዶላር ደረጃ እና ከዚያ በላይ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ዝግጅቶችን የማዘጋጀት ታሪክ ያላቸው ቡድኖች ብቻ ማመልከት ይችላሉ።*

***ከዚህ ቀደም ባለፉት ዓመታት በ$7,200 ዶላር/$7,800 ዶላር ደረጃ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው ከንውኖች/ ፕሮጀክቶች ከሁሉ በአነስተኛው ለ12 ሰኣታት ህዝባዊ የፕሮግራም ዝግጅት[1] አንድ ብቃት የተሰጠው ፓርክ ውስጥ ቢያንስ በሂደት አራት (4) ቀናት ውስጥ[2] ከሚያቀርቡ ክስተቶች/ ፕሮጀክቶች በስተቀር፣ $5,200 ዶላር ወይም ከዚያ በታች የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ያገኛሉ። ይህ ገደብ ከማህበረሰብ በተሰጠ ግብረ-መልስ ላይ የተመሰረተ እና ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ እና ለክስተቶች አቅምን ለማጎልበት እንዲረዳ ነው።*

**ይህ የድጋፍ ገንዘብ መዋጮ ከዚህ በታች በተመለከቱት ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም**

- ለህዝቡ ተደራሽነት የሌላቸው እና ነፃ ያልሆኑ ክስተቶች
- ሃይማኖታዊ አገልግሎቶች
- የድጋፍ ገንዘብ ማሰባሰብ ዋና ዓላማ የሆነባቸው ዝግጅቶች ወይም አቀራረቦች
- ስጦታዎች
- ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው የድርጅቶች አስተዳደራዊ ወጪዎች
- የመሳሪያ ወይም የሶፍትዌር ግዢ
- ከሚፈቀደው 10% በላይ ከምግብ ጋር የተዛመዱ ወጪዎች

## ***<u>የግምገማ መስፈርት</u>***

ለፕሮግራሙ የተረከቡ የሀሳብ አቅርቦቶች በሚከተሉት መስፈርቶች ይገመገማሉ (**በአጠቃላይ 50 ነጥብ**):

- **የፕሮጀክት ጥንካሬ (20 ነጥቦች):** የኪነቶች ተሳትፎን እና የማህበረሰብ ግንኙነቶችን ትርጉም ባለው እና ልዩ በሆኑ ልምዶች/ ገጠመኞች በኩል የሚያበረታታ ግልጽ፣ በሚገባ የታሰበ ክስተት። ከባህላዊ ማህበረሰብ፣ ተጐራባች ሰፈር ወይም ሌላ ፍላጎት ካለው ማህበረሰብ ጋር ያለውን አንድ ትክክለኛ ግንኙነት ያሳያል።
- **የማህበረሰብ ተጽእኖ (20 ነጥቦች):** የፕሮጀክት እቅዱ ሁሉን አቀፍ ለመሆን ትርጉም ያላቸው ጥረቶችን ይገልጻል፣ ማህበረሰብን ያጐለብታል፣ ተሳትፎን ያበረታታል፣ ልዩነቶች ያለውን ታዳሚ ይደርሳል እና በተለይም በመዋቅራዊ ዘረኝነት እና ጭቆና እጅግ ለተጎዱት ተደራሽነትን ይፈጥራል።

- **አዋጭነት (10 ነጥብ):** የሚያደራጀው ቡድን/ግለሰብ ይህንን እና/ወይም ሌላ ክስተት(ቶችን) ለማቅረብ ወይም በሌላ መልኩ ፕሮጀክቱን በተሳካ ሁኔታ የማስፈፀም አቅምን የሚያመለክት የተረጋገጠ የታሪክ መዝገብ አለው፤ የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ድጋፍ ማስረጃ፤ እና ለክስተቱ ግልጽ እውነተኛነት ያለው በጀት።
- ***ተመራጭ ፓርኮች:*** በሕዝቡ በተጨማሪ ተጠቃሚ በመሆን በተለይ ሊያተርፍ ስለሚችል፣ በዝርዝሩ ውስጥ በተጠቀሱት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የተመረጡ ፓርኮች ውስጥ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

## ***<u>የማመልከቻ አጭር መግለጫ እና የአካል ይዘቶች</u>***

*በ2021 ውስጥ የሲያትል ከተማ አዲስ የማመልከቻ ስርዓት FLUXX፣ መጠቀም ጀመረች። እስካሁን ያላደረጉት ከሆነ፣ ማመልከቻውን መክፈት/ ማዳረስ ከመጀመርዎ በፊት አንድ አዲስ አጠቃላይ ገጽታዎትን መፍጠር ያስፈልግዎታል።*

- ***የእውቂያ ግንኙነት/የገንዘብ ስፖንሰር መረጃ:*** *ይህ ክፍል ለዚህ መተግበሪያ የተለየ ሆኖ ነገር ግን በመመዝገቢያው የግል መገለጫ ውስጥ አስቀድሞ ያልተጠየቀ ተጨማሪ የእውቂያ መረጃን ይሰጣል።*
- ***የስነሕዝብ መረጃ:*** *ይህ መረጃ እንደ ማመልከቻዎ አካል ክፍል አይገመገምም ይልቁንም ፕሮግራሞቻችንን የበለጠ ፍትሃዊ እኩልነት ወዳለው ለማድረግ መስራታችንን መቀጠል እንድንችል በፕሮግራሞቻችን ስለምናገለግላቸው ማህበረሰቦች የበለጠ እንድንማር ለመርዳት ነው። ሁሉም ጥያቄዎች በምርጫ ናቸው፣ ነገር ግን ወደ ቀሪው ማመልከቻው ከመቀጠልዎ በፊት መጠይቁ መቅረብ/ መረከብ አለበት።*
- ***የማመልከቻ መረጃ:*** *የተያዙ ቀናቶችን፣ ቦታ/ አድራሻን፣ መጠንን፣ ወዘተ ጨምሮ ከፕሮጀክትዎ ጋር የተዛመዱ አጭር ጥያቄዎች።*
- ***የፕሮጀክት መረጃ:*** *የእነዚህ ጥያቄዎች አላማ ስለ እርስዎ ክስተት/ፕሮጀክት፣ ይህ ክስተት ስለሚያገለግለው ማህበረሰብ እና ስለራስዎ ስላለፉት አንዳንድ መረጃዎችን ለማካፈል ነው።*
    1. **የፕሮጀክት ርዕስ:** የክስተትዎ ስም
    2. **የፕሮጀክት አጭር መግለጫ:** የክስተትዎ ወይም የፕሮጀክትዎ አጭር መግለጫ (ለምሳሌ፣ በአንድ የማህበረሰብ የቀን መቁጠሪያ ላይ የምያስቀምጡት ጥቂት ነገር)።
    3. **የፕሮጀክት መግለጫ:** የገንዘብ ድጋፎች እንዲደረግለት የፈለጉለትን ሥርዐተ በዓሉን፣ የዝግጅቱን ወይም ፕሮጀክት እንቅስቃሴዎችን ይግለጹ። በፕሮጀክትዎ ወይም በክስተትዎ ውስጥ ኪነ ጥበብ እና ባህል እንዴት ተለይተው እንደሚታዩ መረጃን ያካትቱ።
    4. **በኪነጥበብ እና በባህል ማህበረሰብ መገንባት** : እባኮትን ዝግጅትዎን ማን እንደሚሳተፈው ይግለጹ። የእርስዎ ፕሮጀክት ኪነ ጥበብን እና ባህልን እንዴት ማህበረሰብን ለመገንባት ይጠቀማል? አካታችነት ያለው ለመሆን፣ የብዝሃን/ የተለያዩ ህዝቦችን ለማሳተፍ እና ተደራሽነትን ለመጨመር ጥረቶችዎ ምን እንደሚሆኑ ይግለጹ።
    5. ***ዳራ/ ያለፈ ሂደት እና አቅም***: የእርስዎን የኪነ ጥበብ ፕሮግራም ማዘጋጀትን እና የማቅረቢያ እንቅስቃሴዎችን አንድ አጠር ያለ ታሪክ ያቅርቡ። የክስተትዎን ስኬት እንዴት አድርገው ያረጋግጣሉ? ይህ ፕሮጀክት ወይም ክስተት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የሚረዱትን ማንኛውንም ቁልፍ ሽርክናዎች (ከድርጅቶች፣ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ጋር) ይግለጹ።
- **በጀት: የፕሮጀክቱን የበጀት አብነቱን** ሞልተው እና ይስቀሉ ( በኪነት በመናፈሻዎች ውስጥ (Arts in Parks) ድረ-ገጽ ላይ በ"Materials" ስር የተገናኘ)። በ2023 ውስጥ ባጀትዎ የክስተቱን ወጪ የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት፣ ገቢ እና ወጪዎች መመዛዘን አለባቸው፣ እና ማንኛውም የተለገሱ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካተት አለባቸው። እንዲሁም ስለ በጀትዎ ደግሞ አንዳንድ ማስታወሻዎችን ለማካተት የሚያስችል ቦታም አለ።